የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

፴፩ኛ ዓመት ቁጥር ፶፬ አዲስ አበባ
ሰኔ ፲፪ ቀን ፪ሺ፲፯ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

31st Year No. 54
ADDIS ABABA, 19th June, 2025


## ማውጫ


አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፹፭/፪ሺ፲፯

ለሴቶች እና ልጃገረዶች ጤና የተቀናጀ፣ ጠንካራ እና በፈጠራ እና በቴክኖሎጂ የታገዘ አገልግሎት አሰጣጥን ለማሻሻል ከዓለምዓቀፍ የልማት ማህበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ……………………………….....ገጽ ፲፰ሺ፱፻፹፱


## Content


Proclamation No. 1385/2017

International Development Association Loan Agreement for financing Innovative Systems to Promote Integrated, Resilient and Enhanced Response to Women and Girls' Health Project Ratification Proclamation… …...............................................Page 18989


### አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፹፭/፪ሺ፲፯

**በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለምዓቀፍ የልማት ማህበር መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ**

ለሴቶች እና ልጃገረዶች ጤና የተቀናጀ፣ ጠንካራ እና በፈጠራ እና በቴክኖሎጂ የታገዘ አገልግሎት አሰጣጥን ለማሻሻል የሚውል አርባ አምስት ሚሊዮን አንድ መቶ ሺ ኤስ ዲ አር (፵፭ሚሊዮን፩፻ሺ ኤስ ዲ አር) የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለምዓቀፍ የልማት ማህበር መካከል የካቲት ፲፮ ቀን ፪ሺ፲፯ ዓ.ም የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ግንቦት ፳፮ ቀን ፪ሺ፲፯ ዓ.ም በአካሄደዉ ፴፫ኛ መደበኛ ስብሰባ ያጸደቀዉ በመሆኑ፤

### PROCLAMATION NO. 1385/2025

**A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND INTERNATIONAL DEVELOPMENT ASSOCIATION**

**WHEREAS,** the Loan Agreement between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and International Development Association stipulating that International Development Association shall provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Loan an amount equivalent to Forty-Five Million and One Hundred Thousand Special Drawing Rights (SDR 45,100,000) for financing Innovative Systems to Promote Integrated, Resilient and Enhanced Response to Women and Girls' Health Project was signed on the 23rd day of February 2025;

**WHEREAS**, the house of peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said loan agreement at its 33rd regular session held on 3rd day of June 2025;

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

፩. **<u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ "ለሴቶች እና ልጃገረዶች ጤና የተቀናጀ፣ ጠንካራ እና በፈጠራ እና በቴክኖሎጂ የታገዘ አገልግሎት አሰጣጥን ለማሻሻል ከዓለምዓቀፍ የልማት ማህበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፹፭/፪ሺ፲፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. **<u>የስምምነቱ መፅደቅ</u>**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለምዓቀፍ የልማት ማህበር መካከል የካቲት ፲፮ ቀን ፪ሺ፲፯ ዓ.ም የተፈረመው የብድር ስምምነት ቁጥር 7687-ET በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

፫. **<u>የገንዘብ ሚኒስቴር ሥልጣን</u>**

የገንዘብ ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን አርባ አምስት ሚሊዮን አንድ መቶ ሺ ኤስዲአር (፵፭ሚሊዮን፩፻ሺ ኤስ ዲ አር) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

፬. **<u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሰኔ ፲፪ ቀን ፪ሺ፲፯ ዓ.ም**

**ታዬ አጽቀ ሥላሴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**NOW, THERFORE,** in accordance with Article 55 Sub-Articles (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

1. **<u>Short Title</u>**

This Proclamation may be cited as the "International Development Association Loan Agreement for financing Innovative Systems to Promote Integrated, Resilient and Enhanced Response to Women and Girls' Health Project Ratification Proclamation No. 1385/2025".

2. **<u>Ratification of the Agreement</u>**

The Loan Agreement Credit Number 7687-ET signed on the 23rd day of February 2025 between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and International Development Association is hereby ratified.

3. **<u>Power of the Ministry of Finance</u>**

The Ministry of Finance is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Loan an equivalent to Forty-Five Million and One Hundred Thousand Special Drawing Rights (SDR 45,100,000) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

4. **<u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall enter into force upon its publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, on this 19th Day of June, 2025**

**TAYE ATSKE- SELASSIE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**